# ጃርዲያሲስ

## ጃርዲያሲስምንድን ነው?

ጃርዲያሲስ *ጃርዲያ* በሚባል ጥቃቅን ተውሳኮች የሚመጣ የተቅማጥ በሽታ ነው። በመላው ዩናይትድ ስቴትስ እና በመላው ዓለም የተለመደ ለተቅማጥ መንስኤ ነው።

## ጃርዲያሲስ የሚይዘው ማንን ነው?

ማንኛውም ሰው የጃርዲያሲስ በሽታ ሊያዝ ይችላል፣ ነገር ግን በሕፃናት ማቆያ ማዕከላት፣ ዓለም አቀፍ ተጓዦች ላይ እና በትክክል ያልታከመ የመሬት ውሃ በሚጠጡ ሰዎች ላይ (ለምሳሌ ከጅረት የሚጠጡ ተጓዦች ወይም ወንዝ ወይም ሀይቅ ውስጥ ሲዋኙ ውሃ በሚውጡ ሰዎች ላይ በብዛት ይከሰታል) ።

## ጃርዲያሲስ እንዴት ይተላለፋል?

የ*ጃርዲያ* ጥገኛ ተውሳክ በተያዙ ሰዎች እና እንስሳት (እንደ ድመቶች፣ ውሾች፣ አጋዘን፣ ከብቶች እና ቢቨር) ሰገራ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ሰገራቸውም ገጽን፣ ምግብን ወይም ውሃን ሊበክል ይችላል።. ሰዎች የተበከለውን ምግብ በመመገብ ወይም ውሃ በመጠጣት ወይም የተበከሉ በታዎችን (እንደ መጫወቻዎች፣ ዳይፐር ወዘተ) ከነኩ በኋላ እጃቸውን ወደ አፋቸው በማስገባት ይታመማሉ።

## የጃርዲያሲስ ምልክቶች ምንድ ናቸው?

በ*ጃርዲያ* የተያዙ አንዳንድ ሰዎች ምንም አይነት ምልክት የላቸውም። ሌሎች ከቀላል እስከ ከባድ የአንጀት ምልክቶች ያጋጥማቸዋል። ተቅማጥ ለብዙ ሳምንታት ወይም ወራት ሊቆይ ይችላል፣ይህም የክብደት መቀነስ እና የሰውነት ድርቀትን ያስከትላል። የአየማስወጣት፣ ቅባታማ ሰገራ እና የሆድ ቁርጠት ምልክቶችም ሊከሰቱ ይችላሉ።

## የበሽታው ምልክቶች፣ ለበሽታው ከተጋለጡ ከስንት ጊዜ በኋላ ይታያሉ?

የበሽታው ምልክቶች ከተጋለጡ ከ3-25 ቀናት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ። ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ከተጋለጡ ከ 7 እስከ 10 ቀናት ውስጥ ይታያሉ።

## ጃርዲያስ እንዴት ይታከማል?

ምርመራውን ለማድረግ የሰገራ ናሙና በመውሰድ በቤተ ሙከራ ውስጥ መሞከር አለበት። በሰገራ ውስጥ የሚገኙት *ጃርዲያ* ጥገኛ ተሕዋስያን ቁጥር ከቀን ወደ ቀን ስለሚለዋወጥ በርካታ የሰገራ ናሙናዎች መወሰድ አለባቸው።

## ለጃርዲያሲስ ሕክምናው ምንድ ነው?

የጃርዲያ በሽታ ላለባቸው ሰዎች ብዙ ፈሳሽ መጠጣት በጣም አስፈላጊ ነው። በበሽታው ምክንያት ከመጠን በላይ ፈሳሽ በመውጣቱ የሰውነት ድርቀት በጃርዲያሲስ ሊከሰት ይችላል። በተለይም ለህፃናት እና ለነፍሰ ጡር ሴቶች አደገኛ ነው። ሕመሙ ሲጀምሮ አቅራቢዎ ካሉ የጤና ባለሙያዎችን ያማክሩ። ይህንን በሽታ ለማከም አንዳንድ ጊዜ በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች ይመከራሉ።

## ጃርዲያሲስን እንዴት መከላከል ይቻላል?

- ሽንት ቤት ከተጠቀሙ ወይም ዳይፐር ከቀየሩ፣ ምግብ ከማዘጋጀትዎ በፊት እና በኋላ እንዲሁም ከእንስሳት ጋር ከተነካኩ በኋላ እጅን በሳሙና እና በውሃ በጥንቃቄ ይታጠቡ።

- በአግባቡ ያልተጣራ ውሃ ከመጠጣት መቆጠብ። ከተፈጥሮ የውሃ ምንጮች ሲጠቱ ለምሳሌ በእግር ጉዞ ላይ አልያም በካምፕ ውስጥ ፣ ውሃውን ያጣሩ ወይም ያፍሉ ።

- ሁሉንም የውሃ ምንጮች በእንስሳት ወይም በሰው ሰገራ እንዳይበከሉ ይጠብቁ። ካምፕ በሚያደርጉበት ጊዜ ወይም በሌላ መንገድ የንፅህና መጠበቂያዎችን መጠቀም በማይችሉበት ጊዜ የውጪ የውሃ መስመሮችን ከመበከል ለመከላከል የፍሳሽ ቆሻሻን በጥንቃቄ ያስወግዱ።

- በግብረ *ሥጋ* ግንኙነት ወቅት የሰገራ ንክኪን እና መበከልን መከላከል።

## በቫይረሱ የተያዘ ሰው *ጃርዲያ* ጥገኛ ተውሳኮችን እስከ መቼ ሊሸከም ይችላል?

ሰዎች በሰገራቸዉ ውስጥ ከተወሰኑ ሳምንታት እስከ ጥቂት ወራት *ጃርዲያ* ሊያስወጡ ይችላሉ። ሕክምናው በህመሙን ጊዜ ሊያሳጥር ይችላል እና ተህዋሲያን በሰገራ ውስጥ የሚቆይበትን ጊዜ ያሳጥራል።

**በበሽታው የተያዘ ሰው ከስራ ወይም ከትምህርት ቤት መገለል አለበት?**

ተቅማጥ ያለባቸው ሰዎች ለሌሎች አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉበት ከልጆች እንክብካቤ መስጫ፣ ከታካሚ እንክብካቤ መስጫ ወይም ከምግብ አያያዝ መገለል አለባቸው። ከእያንዳንዱ የሽንት ቤት ጉብኝት በኋላ፣ ዳይፐር ከቀየሩ በኋላ እና ምግብ ከማዘጋጀት በፊት እጃቸውን በሳሙና እና በውሃ በጥንቃቄ ከታጠቡ አብዛኛው ሰው ተቅማጡ ሲቆም ወደ ስራ ወይም ትምህርት ቤት ሊመለሱ ይችላሉ። የጤና ክፍሉ በበሽታው የተያዘው ሰው የምግብ ተቆጣጣሪ፣ የጤና እንክብካቤ ሰራተኛ፣ ወይም የህጻናት እንክብካቤ ሰራተኛ በሆነበት አጋጣሚ የተለየ የምክር አገልግሎት ይሰጣል።

## ስለ ጃርዲያሲስ እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- ስለ ጃርዲያሲስ ስጋት ካሎት በአቅራቢዎ የሚገኝ የጤና ባለሙያ ያነጋግሩ።

- ለአካባቢዎ የጤና መምሪያ ይደውሉ። የአካባቢያዊ የጤና መምሪያዎች ማውጫ እዚህ ይገኛል፦http://www.vdh.virginia.gov/local-health-districts/።

- የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከልን በ http://www.cdc.gov/parasites/giardiaላይ ይጎብኙ።

ሴፕቴምበር 2018